# በታክስና በጉሙሩክ ቀረጥ አሠራር ላይ የሚታዩ ችግሮች፤

# የችግሮቹ መንስዔና የመፍትሔ ኃሳቦች

# 1. የገቢ ግብር ልክ አወሳሰን ፡

ሀ) **መንስዔው**

አልፎ አልፎ የሚከሰት በዴስክ-ኦዲት ላይ ብቻ የተመሠረተ የግብር ልክ ውሳኔ ያስከተለው ችግር

- የታክስ ፍትሐዊነት መርህ መጣሱ
- አሰራሩ ግልጽነት የጐደለውና ለመገመት አዳጋች መሆኑ፣

የመፍትሔ ኃሳብ፣

- የአዋጁን ድንጋጌዎች አሟልተው የሚገኙ ታክስ ከፋዮች የሚከፍሉት ግብር በዴስክ ኦዲት ላይ ብቻ ሳይወሰን የሂሳብ መዝገቦቻቸውም ተመርምረው የግብር ልክ መወሰን አለበት፡፡

ለ) ስለተቀናሽ ሂሳቦች

**የችግሩ መንስዔ**

በገቢ ግብር ኣዋጁ አንቀጽ 21 ላይ በግብር ስሌት ወቅት ወጪያቸው ተቀናሽ እንደማይደረግ በዝርዝር ከተቀመጡት ውጭ ያሉ ሌሎች ወጪዎች ተቀናሽ አለመደረጋቸው፡፡

**ያስከተለው ችግር**

በአዋጁ በተደነገገው መሠረት ተቀናሽ የሚደረጉ ወጪዎችን አለመቀበል የታክስን የእርግጠኝነትና ተገማችነት መርህ የሚጥስ መሆኑ፤

**የመፍትሔ ኃሳብ**

በአዋጁ አንቀጽ 21 ላይ እነደተመለከተው በግብር ስሌት ወቅት ተቀናሽ የማይደረጉ ወጪዎች በዝርዝር ተቀምጠዋል፡፡ በአዋጁ ከተደነገጉት ተቀናሽ ከማይደረጉ ወጪዎች በስተቀር ሌሎች ወጪዎች ተቀናሽ የሚደረጉ በመሆናቸው በአዋጁ ተቀናሽ እንደማይደረጉ ከተደነገጉት ወጪዎች በስተቀር ከታክስ ከፋዩ የንግድ ሥራ ጋር የተያያዙ ወጪዎች በሙሉ እንደ ወጪ ሊያዙ ይገባል፡፡

# 2. ተጨማሪ እሴት ታክስ

ሀ) **ርዕሰ ጉዳይ**

የተእታ ከፋይነት ምዝገባ ሁሉን አቀፍ አለመሆን

**የችግሩ መንስዔ**

ተመሳሳይ እቃ የሚሸጡ ተቋማት አንዱ የተ.እ.ታ ተመዝጋቢ ሆኖ 15% ጨምሮ ሲሸጥ ሌላው ደግሞ ተርን ኦቨር ታክስ ብቻ ወይም ነፃ ሆኖ ስለሚሸጥ በገበያ ላይ ተገቢ ያልሆነ ውድድርን መፍጠሩ፤

**ያስከተለው ችግር**

በገበያ ላይ ተገቢ ያልሆነ ውድድር መፍጠሩ፤

**የመፍትሔ ኃሳብ**

- አሁን ያለውን የ ተ.እ. ታ. ምጣኔ በማውረድና ከተረን ኦቨር ታክስ ምጣኔም ጨመር በማድረግ አማካይና ወጥ የሆነ የታክስ ምጣኔ መተግበር
- የተእታ ተመዝጋቢ ያልሆኑ ድርጅቶችን እንዲመዘገቡ በማድረግ የገበያ ውድድሩን ፍትሐዊ ማድረግ፤

## ለ) የተፈጻሚነት ወሰን

**የችግሩ መንስዔ**

ከሥራ ባህሪያቸው የተነሳ ደረሰኝ መስጠት የማይችሉ በአነስተኛ ደረጃና በባህላዊ የማምረት ዘዴ የሚጠቀሙ አምራቾች /ድንጋይ፣ እንጨት/ ወ.ዘ.ተ እንዲሁም መዝገብ ለመያዝ የማይገደዱ የደረሕ /ሐ/ ግብር ከፍዮች ለሚሸጧቸው መርቶች በገዥው የክፍያ ቫውቸር ወይንም የግዥ ውል ሰነዶች በተጨማሪ ማረጋገጫነት መጠቀም፣

**ያስከተለው ችግር**

የተእታ ተመዝጋቢ ሳይሆኑ ከሚነግዱ ነጋዴዎች የሚሰጡ ደረሰኞች በግብር ሰብሳቢው ተቀባይነት ማጣት፣

**የመፍትሔ ኃሳብ**

በገዢው የክፍያ ቫዉቸር ወይንም የግዢ ውል ሰነዶች በመጠቀም እቃዎችን የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ከሆኑት ድርጅቶች ብቻ ሳይሆን ተመዝጋቢ ካልሆኑትም ለመግዛት የተገደዱ መሆናቸውን በመገንዘብ ተመዝጋቢ ካልሆኑት ተቋማት መግዛት እየተሰራባቸው ካሉት መመሪያዎች ጋር የማይጋጭ በመሆኑ በዚሁ መሠረት ቢፈፀም::

ሐ) በትራንስፖርት አገልግሎት የተ.እ.ታ. አተገባበር

**የችግሩ መንስዔ**

የትራንስፖርት አገልግሎት ከተ.እ.ታ. ነጻ ቢሆንም በአዋጁ መሠረት አለመሠራቱ፣

**ያስከተለው ችግር**

የገልባጭ መኪና አከራዮች የተ. እ. ታ. እንዲከፍሉ መገደዳቸው፣

**የመፍትሔ ኃሳብ**

አዋጁ በሚፈቅደው መሠረት የትራንስፖርት አገልግሎትን ከተ.እ.ታ. ነፃ ማድረግ፡፡

# 3. የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ

**ርዕሰ ጉዳይ**

የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የመጠቀም ግዴታ

**የችግሩ መንስዔ**

የኮንስትራክሽን ኩባንያዎች፣ አማካሪ ድርጅቶችና የመጠጥ አምራች ኢንዱስትሪዎች የአሻሻጥ ሁኔታና ባህሪያቸው የተለየ ስለሆነ ለአስገዳጅ መመሪያ መዳረጋቸው፣

**ያስከተለው ችግር**

ከላይ የተመለከቱት የሥራ ዘርፎች የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ለመጠቀም በመገደዳቸው ለአላስፈላጊ ወጪና እንግልት መዳረጋቸው።

**የመፍትሔ ሀሳብ**

የንግድ እንቅስቃሴያቸው የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያን ለመጠቀም ያለውን አመቺነት ባገናዘበ መልኩ በደንብ ቁጥር 139/1999 አንቀጽ 3 መሰረት መመሪያ እንዲወጣ ማድረግ።

# 4. የኤክሳይዝ ታክስ

**የችግሩ መንስዔ**

የግብር አብይ መርህ የሆነውን የአመቺነት (Canon of Convenience) በሚጥስ ሁኔታ ከረዥም ጊዜ በኋላ የብዙ ሚሊዮን ውዝፍ ግብር እና መቀጫ በታሸገ ውሃ አምራች ኩባንያዎች ላይ ባልጠበቁት ወቅትና ሁኔታ እንዲከፍሉ መደረጉ ፤

**ያስከተለው ችግር**

የታሸገ ውሃ አምራች ኩባንያዎች ባልተጠበቀና አመቺ ባልሆነ ሁኔታ የኤክሳይዝ ውዝፍ ግብር ከነ መቀጮው እንዲከፍሉ ፤ ያልቻሉት ደግሞ ንብረታቸው በሐራጅ እንዲሸጥ መወሰኑ

**የመፍትሔ ኃሳብ**

- በዚህ መንገድ ግብር ለከፈሉት ተመላሽ፤
- በዚህ ምክንያት ንብረታአዉ በሃራጅ እንዲሸጥ ለተወሰነባቸው ከዕዳ ነፃ መሆናቸውን ማወጅ፤
- እንዲሁም ለወደፊቱ ተገማችና አመቺ አሠራር መኖሩን ማረጋገጥ

# 5. የጉሙሩክ ፍተሻ

**ርዕስ ጉዳይ**

በጉምሩክ ፍተሻ መጓተት

**የችግሩ መንስዔ**

የዕቃዎች አካላዊ ፍተሻ፣ /አዲሱ የጉምሩክ አዋጅና ጉምሩክ የሚጠቀምበት የASYCUDA ሲስተም የሥጋት ሥራ አመራርን ለመጠቀም የሚያስችሉ ቢሆንም፣ የባለሥልጣኑ መ/ቤት ይህንን አሰራር አልዘረጋም/፡፡

**ያስከተለው ችግር**

የወደብ አገልግሎት ችግሮችና የጉምሩክ የመፈተሽ ጣቢያዎች የተጓተቱ አገልግሎቶች በንግድ ህብረተሰብ ላይ አላስፈላጊ ወጪ ማስከተሉ፤

**የመፍትሔ ኃሳብ**

የሥጋት ሥራ አመራር (Risk Management System) ሥርዓትን ተግባራዊ ማድረግ፣

- የድህረ ክሊራንስ ኦዲት አሠራርን ተግባራዊ ማድረግ፣
- የንግድ መረጃ መረብን ተግባራዊ ማድረግ፣
- ዕቃዎች ከመድረሳቸው አስቀድሞ የሰነድ ሥራን ማከናወን፣

# 6. የሞባይል አስመጪዎች ጉዳይ

**ርዕሰ ጉዳይ**

የሞባይል እና ሌሎች አስመጪዎች

**የችግሩ መንስዔ**

የኮንትሮባንድ ንግድና የመንገድ ላይ ንግዶች መስፋፋት፣

**ያስከተለው ችግር**

በኮንትሮባንድ የገቡ ዕቃዎች ከገበያ ዋጋ በታች የሚሸጡ በመሆናቸው የሕጋዊ ነጋዴዎችን የገበያ ተወዳዳሪነት ይጎዳል፡፡

**የመፍትሔ ኃሳብ**

- የመንገድ ላይ ንግድን ሥርዓት ማስያዝ፣
- የኮንትሮባንድና ሕገ ወጥ ንግድን ለመቆጣጠር መንግሥት የጀመረውን ሥራ አጠናክሮ መቀጠል፣
- የመንግስትና የግሉ ዘርፍ ሊተባበሩ ከሚችሉባቸው የትብብር መስኮች አንዱ ዘመናዊ የመከታተያ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ሕገ ወጥ ንግድን መቆጣጠር በመሆኑ ይህን የትብብር ሥራም እንደ ተጨማሪ አማራጭ ማየት፣

# 7. የብረታ ብረት አስመጪዎች ጉዳይ

**ርዕስ ጉዳይ**

የብረት አስመጪዎችን በተመለከተ ስለተላለፈው አዲስ መመሪያ፣

**የችግሩ መንስዔ**

(ZERO TOLERANCE LIMIT) ምንም ዓይነት የሚዛን ጉድለት መኖር እንደሌለበት በመግለጽ ለብረት አስመጪዎች ስለተላለፈው አዲስ መመሪያ፣

**ያስከተለው ችግር**

በብረት አስመጪዎች ላይ አላስፈላጊ የሆነ ሥጋት መፍጠር፣

**የመፍትሔ ኃሳብ**

ተቀባይነት ያለውTOLERANCE LIMIT PROVISION እንዲኖር ማድረግ፣

# 8. የግብር አቤቱታ/ቅሬታ አፈታት

**የችግሩ መንስዔ**

የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዳኛም ከሳሽም ሆኖ መሥራቱ፣

**ያስከተለው ችግር**

በግብር ጉዳይ የንግዱ ማህበረሰብ ነፃና ገለልተኛ የሆነ ዳኝነት ማጣቱ፣

**የመፍትሔ ኃሳብ**

- ወገንተኛ ያልሆነ ያሠራር ሥርዓት መዘርጋት፤
- በየደረጃው በተቋቋመው የግብር አቤቱታና ቅሬታ ተቀባይ ኮሚቴዎች ውስጥ የንግዱ ኅብረተሰብ ተወካዮችን ማሳተፍ